## የዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ሲፒርየር ፍርድ ቤት

## በዋና ዳኛ (ቺፍ ጃጅ) ጀሰ-ሀሪንግ የተላለፈ ትዕዛዝ

## (በ6/10/2022 የተሻሻለ)

ይህ ትእዛዝ እስከ ጁላይ 31፣ 2022 ድረስ ተፈጻሚ ይሆናል። ከኦገስት 1፣ 2022 ጀምሮ በአንጻራዊነት በቅርቡ በሚለቀቀው ሲፒርየር ፍርድ ቤቱን ዳግም-ለማሰላሰል (ሪኢማጂኒንግ) ከተያዘው እቅድ ጋር በተጣጣመ መልኩ ስራዎች ይከናወናሉ።

በማርች 18፣ 2020 በተላለፈውና በመይ 29፣ 2020 ዳግም በተረጋገጠው ትእዛዝ መሰረት፣ ጆይንት ኮሚቲ ኦን ጁዲሽያል አድሚኒስትሬሽን (የፍትህ አስተዳደር የጋራ ኮሚቴ) አሁን ባለው የዳኝነት አስቸኳይ ጊዜና ለፍትህ አስተዳደርም የተሻለ ስለሆነ፣ በዲ.ሲ. ኮድ እና በሱፒርየር ፍርድ ቤት ደንቦች ያሉ ሁሉም የህግና ደንብ-ተኮር የጊዜ ገደቦች ታግደው፣ ለጊዜው ከተፈጻሚነት ቆመው (ቶል ተደርገው) እና ተራዝመው የሚቆዩበት የጊዜ ገደብ ለማራዘም የሚያስችሉ ትእዛዞች የማስተላለፍ ስልጣን ለዋናው ዳኛ (ቺፍ ጃጅ) ሰጥቷል። በማርች 18፣ 2020፣ በማርች 19፣ 2020፣ በመይ 14፣ 2020፣ በጁን 19፣ 2020፣ በኦገስት 13፣ 2020፣ በኖቬምበር 5፣ 2020፣ በጃንዋሪ 13፣ 2021፣ በማርች 30፣ 2021፣ በመይ 12፣ 2021 በጁላይ 14፣ 2021፣ በሰፕተምበር 11፣ 2021፣ በኖቬምበር 21፣ 2021 እና ኤፕሪል 8፣ 2022 በተላለፉት ትእዛዞች፣ ዋናው ዳኛ (ቺፍ ጃጅ) እንደሚከተለው ብሎ ነበር፡ (በግልጽ ካልተጠቀሰ በስተቀር) ሁሉም ከኤፕሪል 8፣ 2022 በፊት እንዲፈጸሙ በህጎች፣ በፍርድ ቤት ደንቦች፣ እና ፍርድ ቤት ባስተላለፋቸውና በሌሎች ትእዛዞች የሰፈሩ የጊዜ ገደቦች፣ የአሁኑ የዳኝነት አስቸኳይ ጊዜ (ጁዲሽያል ኢመርጀንሲ) ተፈጻሚ እስከሚሆንበት ጊዜ ድረስ ይታገዱ፣ ከተፈጻሚነት ለጊዜው ይቆሙ (ቶል ይደረጉ)፣ እንዲሁም ደግሞ ይራዘሙ ዘንድ ታዝዞ ነበር። በትእዛዙ እንደተመለከተው፣ የጊዜ ገደቦቹ፣ ሁኔታዎች ሲቀየሩ ለተጨማሪ ጊዜ ሊታገዱ፣ ከተፈጻሚነት ለጊዜው ሊቆሙ (ቶል ሊደረጉ)፣ እንዲሁም ደግሞ ሊራዘሙ ይችላሉ። እገዳው፣ ከተፈጻሚነት ለጊዜው መቆሙ (ቶል መደረጉ)፣ እና መራዘሙ፣ በዚህ ትእዛዝ ውስጥ ካልሰፈረ በስተቀር በጁን 10፣ 2022 ያቆማል።

የኮቪድ-19 ምልክቶች ያለባቸው ጠበቆችም ይሁን ሰዎች ወደ ፍርድ ቤት መግባት የለባቸውም። https://www.cdc.gov/coronavirus/2019-ncov/about/symptoms.html ይመልከቱ።

ሁሉም ወደ የሱፒርየር ፍርድ ቤት ህንጻ የሚገቡ ሰዎች አፍንጫ እና አፍ የሚሸፍን ጭንብል (ማስክ) ማድረግ ይኖርባቸዋል። Order Requiring Persons To Wear Cloth Face Coverings In Court Buildings During The Covid-19 Pandemic (በኮቪድ-19 ወረርሽኝ ጊዜ ሰዎች ወደ ፍርድ ቤት ህንጻ ሲገቡ የጨርቅ የፊት መሸፈኛ እንዲያደርጉ የሚያስገድድ ትእዛዝ) ይመልከቱ።

## የፍትሐብሔር ክፍል (ሲቪል ዲቪዥን)

በማህበረሰብ ጤና አስቸኳይ ጊዜ ህጋዊ ክልከላ (ስታቹቶሪ ሞራቶርየም) የሚመለከታቸው የይገባኛል ጥያቄዎች ክስ የሚቀርብባቸው የጊዜ ገደቦች (ስታቹ ኦፍ ሊሚቴሽንስ) ህጋዊ ክልከላ (ስታቹቶሪ ሞራቶርየም) በስራ ላይ እስካለ ድረስ ይታገዳሉ፣ ለጊዜው ከተፈጻሚነት ይቆማሉ (ቶል ይደረጋሉ)፣ ይራዘማሉም።

ማናቸውም የአስቸኳይ ማመልከቻ (ኢመርጀንሲ ሞሽን) ወደ Civilefilings@dcsc.gov ኢመይል በማድረግ በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ ፋይል መደረግ ይኖርበታል።

የፋይል ማድረጊያ ክፍያ ይተውልኝ ማመልከቻዎች (አፕሊኬሽን ፎር ፊ ወይቨርስ) እና ማናቸውም ከማመልከቻው ጋር ፋይል የሚደረግ ወደ Civilefilings@dcsc.gov ኢመይል በማድረግ በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ ፋይል መደረግ ይኖርበታል።

አስተዳደራዊ ትዕዛዝ 06-17 (አድሚኒስትሬቲቭ ኦርደር 06-17) ምን ይበል ምን፣ የመጥሪያ ማድረሻ ቃለ መሀላዎች (አፊዳቪትስ ኦፍ ሰርቪስ) በአስቸኳይ ጊዜ ወቅት በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ ፋይል ሊደረጉ ይችላሉ።

አስተዳደራዊ ትዕዛዝ 15-03 (አድሚኒስትሬቲቭ ኦርደር 15-03) ምን ይበል ምን፣ የመኖሪያ ቤት ሁኔታ ጥሰቶች መዝገቦችና፣ እንደነ ወሳኝ ኩነት ሰነዶችን ለማሻሻል የሚቀርቡ ማመልከቻዎች፣ የስም ለውጦች፣ የጾታ ምደባዎች (ጀንደር አሳይመንትስ)፣ የውጭ አገር የፍርድ ቤት መጥሪያ (ፎረይን ሰፒና)፣ የፍትሐብሔር የንብረት መውረስ (አሰት ፎርፈይቸር) አቤቱታዎች፣ የመረጃ ስም ማጥፋት (ሊበልስ ኦፍ ኢንፎርሜሽን)፣ እና ጓዳዊ ክሶች (ፍርየንድሊ ሱትስ) ጨምሮ ሁሉም በጃጅ-ኢን-ቻምበርስ የሚሰሙ መዝገቦች በአስቸኳይ ጊዜ ወቅት በኬዝ ፋይል ኤክስፕረስ (CaseFileXpress) በኩል በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ ፋይል ሊደረጉ ይችላሉ።

ደንብ 5 እና 5-III የሰፈረው ምን ይሁን ምን፣ ታትመው ያሉ (ሲልድ) መዝገቦችና በመዝገብ ቁጥራቸው SLD የሚል ያለባቸው (ለምሳሌ፡ 2020 CABSLD 000001)፣ በአስቸኳይ ጊዜ ወቅት ሰነዶች በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ ፋይል መደረግ ይችላሉ። ባልታተመ (አንሲልድ) መዝገብ፣ የታተሙና (ሲልድ) ያልተቀነሰባቸው (አንሪዳክትድ) ሰነዶች ወደ ጸሀፊ ቢሮ (ክለርክስ ኦፊስ) በአካል፣ በወረቀት በፖስታ ወይም በመጣያ ሳጥን (ድራፕ ባክስ) በኩል ማስረከቡ መቀጠል ይኖርባቸዋል።

## የወንጀለኛ ክፍል (ክሪሚናል ዲቪዥን)

ከሰፕተምበር 6፣ 2022 ጀምሮ ፍርድ ቤቱ በእስር የሌሉ መዝገቦች የ9-ወር የክስ የጊዜ መስመር (ኢንዳይክትመንት ታይምላይን) ከተፈጻሚነት ማቆሙን ያቆማል (Rule 48 (c)(1), D.C. Code § 23-102)።

ከማርች 15፣ 2020 ጀምሮ፣ በ§ D.C. Code 11-947(c) መሰረት ከላይ ያሉትን የጊዜ መስመሮች መጀመሪያ ከተፈጻሚነት ካቆሙት ቀን ያለውን ክፍለ ጊዜ ጀምሮ፣ እስከ ከተፈጻሚነት የሚቆምበት ጊዜ ድረስ ያሉትን ቀናት፣ የክስ (ኢንዳይትመንት)፣ ክርክር፣ ወይም ሌሎች ተዛማጅ የጊዜ ገደቦች ስሌት ላይ መካተት የለባቸውም።

ከጁላይ 18፣ 2022 ጀምሮ የሱፒርየር ፍርድ ቤት የአደንዛዥ ዕጽ ጣልቃ ገብነት ፕሮግራም (ድራግ ኮርት) እና የአእምሮ ጤና ማህበረሰብ ፍርድ ቤት (ሜንታል ሄልዝ ኮሚዩኒቲ ኮርት) ችሎቶች በአካል ወደ መካሄድ ይመለሳሉ። ዳኛ፣ ተገቢ ሆኖ ካገኘው፣ የተወሰኑ በርቀት መቅረቦችን መፍቀድ ይችላል።

የወንጀለኛ ክፍል እንደሚከተለው ይሰራል፡

- ተጨማሪ ማስታወቂያ እስኪሰጥ ድረስ የሚከተሉት ቀጠሮዎች ሙሉ በሙሉ በርቀት የሚከናወኑ ሲሆን ሁሉም ተከራካሪ ወገኖች በተቻላቸው መጠን በቪድዮ መቅረብ ይኖርባቸዋል፣ በቪድዮ መቅረብ የማይችሉ ከሆነ ግን በቴሌፎን መቅረብ ይችላሉ። በርቀት ችሎት መቅረብ የማይችሉ ግለሰቦች ለቀጠሮአቸው እንዴት በርቀት መግባት እንደሚችሉ መረጃ ለማግኘት ወደ ፍርድ ቤቱ መረጃ ዴስክ መምጣት ይችላሉ።
    - ዩ.ኤስ.ኤ.ኦ./ኦ.ኤ.ጂ. የጥቅስ የእምነት ክህደት እና አቅጣጫ መቀየርያ ካላንደር (ሳይቴሽን አረይንመንት ኤንድ ዳይቨርዥን ካላንደር)
- የእምነት ክህደት ችሎቶች (አረይንመንትስ) እና መቅረቦች (ፕረዘንትመንትስ) በፍርድ ቤት ክፍል ቁጥር C-10 ይሰማሉ። በC-10 የተመደቡ የመንግስት ጠበቆችና የሲ.ጀይ.ኤ. ተጠባባቂ ጠበቆች በአካል ይቀርባሉ። በተለየ መልኩ የተመደቡ የመንግስትና የተከላካይ ጠበቆች በርቀት መቅረብ ይችላሉ። በዲ.ሲ. እስር ቤት (ጀይል) ያሉ ተከላካዮች በቪድዮ መቅረቡን ይቀጥላሉ። እንዲታሰሩ ያልተጠየቀባቸው ተከላካዮች እስከ ተቻለ ድረስ በርቀት መቅረቡን ይቀጥላሉ። ወደ ተከሰሶውበት የነበረ ክልል መመለሻ ችሎቶች (ኤክስትራዲሽን ሂሪንግስ) በዋና ዳኛ (ቺፍ ጃጅ) ቀጠሮ ይያዝላቸዋል። ከዚህ ትዕዛዝ ውጪ የሆኑ ተጨማሪ ለውጦች ይመጣሉ።

- ሁሉም በእስር-የሌሉና በእስር ያሉ መዝገቦች በተመደበው የቀላል ወንጀል የማህበረሰብ ፍርድ ቤት (ሚስደሚነር ኮሚዩኒቲ ኮርት) እና በከባድ ወንጀል ካላንደሮች (ፌለኒ ካላንደርስ) በተመደበላቸው የፍርድ ቤት ክፍል በርቀትና በአካል መከናወኑ ይቀጥላሉ።

- ሁሉም የፍርድ ቤት ክፍሎች፣ የተከላካዮች፣ ምስክሮች፣ ተበዳዮች፣ ጠበቆች፣ የፍርድ ቤት ሰራተኞች፣ ጁረሮች እና ሌሎች የማህበረሰቡ አባላት ጤናና ደህንነት በሚጠብቅ መልክ በአካልና በርቀት ለማሳተፍ ተዋቅረዋል።

    - **ከእስር ተፈተው ያሉ ተከላካዮች በተመለከተ፣** ወደ ፍርድ ቤት በተባለው ቀንና ሰአት እመጣለሁ ("ፒ.አር.") በማለት ቃል ገብተው ከእስር የተለቀቁ በቀላል ወንጀል የተከሰሱ እና የሚስማሙ ተከላካዮች በአካል፣ በቪድዮኮንፈረንስ ወይም በቴሌፎን ኮንፈረንስ በድርድር ለተደረጉ ስምምነቶች (ፐሊስ) እና ለፍርድ መቅረብ ይችላሉ። በከባድ ወንጀል ተከስሰው በፒ.አር. ከእስር የተለቀቁ ተከላካዮች እና የሚስማሙ ተከላካዮች በድርድር ለተደረጉ ስምምነቶች (ፐሊስ) በቪድዮ ኮንፈረንስ መቅረብ ይችላሉ።
    - ለክርክር (ትራያል)፣ እና እስር እና ቅድሚያ ችሎቶች (ዲተንሽን ኤንድ ፕረሊሚናሪ ሂሪንግስ)፣ እና ስምምነት ያልተደረሰበት ማስረጃ የሚሰማባቸው ችሎቶች (በህግ የሚፈቀድ ከሆነና በርቀት ለመቅረብ በስምምነት ላይ ካልተደረሰ በስተቀር) ካልሆኑ በስተቀር፣ **በዲፓርትመንት ኦፍ ሪሃብሊቴሽን ሰርቪስስ (በተሀድሶ አገልግሎቶች ክፍል)፣ በእስር ቤቶች ቢሮ (ቢሮ ኦፍ ፕሪዝንስ)፣ እና በዲፓርትመንት ኦፍ ቢሄቭየራል ሄልዝ (የባህርይ ጤና ክፍል) ስር ያሉ ተከላካዮች በርቀት መቅረቡን መቀጠል ይችላሉ።**
    - ተከላካይ በችሎት የመቅረብ መብቴን በገዛ ፈቃዴ እተዋለሁ ካላለ፣ ወይም ተከላካይ በቪድዮ መቅረቡን እስማማለሁ ካላለ በስተቀር **በዲፓርትመንት ኦፍ ኮሬክሽንስ (በማረሚያ ቤት ክፍል) ስር በከባድ ወንጀል እና ቀላል ወንጀል መዝገቦች ያሉ ተከላካዮች በአካል ይቀርባሉ።**
    - ተከላካዩ በቪድዮ የሚቀርብ ከሆነ **የመንግስትና የተከላካይ ጠበቆች** በቪድዮ መቅረብ ይችላሉ።
    - ተከላካዩ በአካል የሚቀርብ ከሆነ፣ የተመደበው ዳኛ ሌላ ካልፈቀደ በስተቀር፣ **የመንግስትና የተከላካይ ጠበቆች** በአካል ይቀርባሉ።
    - በግለሰብ መዝገብ በርቀት ምስክርነት እንዲሰጡ ፍርድ ቤቱ ካልፈቀደ በስተቀር በሁሉም ሂደቶች ያሉ **ምስክሮች** በአካል መቅረብ ይኖርባቸዋል።
    - **የቅድመ ክርክር አገልግሎቶች (ፕሪትራያል ሰርቪስስ) እና የፍርድ ቤት አገልግሎቶች እና የበዳይ ክትትል ኤጀንሲ ተወካዮች** በአካል መሳተፍ ይችላሉ፣ ነገር ግን ከተቻለ በርቀት በቪድዮ፣ በቪድዮ መቅረብ የማይችሉ ከሆነ ደግሞ በቴሌፎን እንዲቀርቡ ይበረታታሉ። በቪድዮ መቅረቡ በይበልጥ ይበረታታል።

- **የወንጀል ሰለባዎች** በአካል መሳተፍ ይችላሉ፣ ነገር ግን ከተቻለ በርቀት በቪድዮ ወይም በቴሌፎን እንዲቀርቡ ይበረታታሉ።

- **ባጠቃላይ፣ የህብረተሰቡ አባላት** ችሎቶቹን የመያዝ አቅም ገደቦች እስከፈቀዱ ድረስ በአካል መሳተፍ ይችላሉ፣ ነገር ግን የሚቻል ከሆነ ቪድዮ ወይም ቴሌፎን በመጠቀም በርቀት እንዲቀርቡ ይበረታታሉ። ነገር ግን **በጁሪ በሚዳኙ ክርክሮች** ክርክሩን መከታተል የሚፈልጉ የማህበረሰቡ አባላት በአካል መቅረብ ይኖርባቸዋል።

## <u>የቤት ውስጥ ሁከት ክፍል (ዶመስቲክ ቫዮለንስ ዲቪዥን)</u>

የቤት ውስጥ ሁከት ክፍል (ዶመስቲክ ቫዮለንስ ዲቪዥን) (ዲ.ቪ.ዲ.) እንደሚከተለው ይሰራል፡

- የቤት ውስጥ ሁከት ክፍል (ዶመስቲክ ቫዮለንስ ዲቪዥን) የጸሀፊ ቢሮ (ክለርክስ ኦፊስ) በአካልና በርቀት ከ8:30 ኤ.ኤም. እስከ 5፡00 ፒ.ኤም. ድረስ ከሰኞ እስከ አርብ ድረስ ይገኛል።

- የማህበረሰቡና የሰራተኞቹ ጤናና ደህንነት ለመጠበቅ የጸሀፊ ቢሮ (ክለርክስ ኦፊስ) ማህበራዊ ርቀት እና የብዛት ገደቦች ይጠቀማል። የተወሰኑ ሰራተኖች በአካል በፍርድ ቤቱ የሚሰሩ ሲሆን ሌሎች ሰራተኞች በርቀት መስራቱን ይቀጥላሉ።

- የፍትሐብሔር ፋይል የሚደረጉ ነገሮች በጸሀፊ ቢሮ (ክለርክስ ኦፊስ) በአካል ወይም በርቀት መደረግ ይችላሉ፡
    1. በበይነ መረብ (ኦንላይን) በwww.probono.net/dccourts፣ ወይም፣
    2. በዲ.ቪ.ዲ. ድረገጽ የሚገኙትን ቅጾች ሞልቶ ወደ DVD@dcsc.gov ኢ-መይል በማድረግ። ሊሞሉ የሚችሉ ቅጾች ለማግኘት በሚከተለው ይጫኑ፡ here (ከዚህ)።

- በዲ.ቪ.ኤም. እና በሲ.ሲ.ሲ. መዝገቦች የወንጀለኛ ፋይል የሚደረጉ ነገሮች ኬዝፋይልኤክስፕረስ በመጠቀም በበይነ መረብ (ኦንላይን) ፋይል ማድረጉ መቀጠል ይኖርባቸዋል።

- ዲ.ቪ.ዲ. በአካልና በቦታ አገልግሎቶች (ኦንሳይት ሰርቪስስ) ባካተተ በቅይጥ ክንውኖች (ሀይብሪድ ኦፐሬሽንስ) ማድረጉን ይቀጥላል። የተወሰኑ ዳኞችና የፍርድ ቤት ሰራተኞች በርቀት መስራቱን ይቀጥላሉ። ተከራካሪ ወገኖች፣ በከፊል በርቀት በሚካሄድ ፍርድ ቤት በአካል እንዲቀርቡ በልዩ ሁኔታ ካልታዘዙ በስተቀር፣ በዲ.ቪ.ዲ. የርቀት ፍርድ ቤቶች (ሪሞት ኮርትሩምስ) በቴሌፎን ወይም ቪድዮኮንፈረንስ መቅረብ መቀጠል ይችላሉ።

- በዲ.ቪ.ዲ. የሚካሄዱ የፍርድ ቤት ሂደቶች ለህዝብ ክፍት ናቸው። ተከራካሪ ወገኖች ወደ ፍርድ ቤት ክፍሉ እንዴት በቀጥታ መግባት እንደሚችሉ መመርያዎች ያገኛሉ። ተከራካሪ ወገኖች-ያልሆኑ የዲ.ቪ. ክፍል የጸሀፊ ቢሮን በ (202) 879-0157 በመደወል ወይም ወደ DVDhearings@dcsc.gov ኢ.መይል በማድረግ ወደሚፈልጉት ፍርድ ቤት ክፍል መግቢያ መረጃ ማግኘት ይችላሉ።

- ስድስት የፍርድ ቤት ክፍሎች በርቀት (ሪሞትሊ) ወይም በቅይጥ (ዳኛ እና ጸሀፊዎች በአካል የሚገኙ ሲሆን እንደየ መዝገቡ የተወሰኑ ተከራካሪ ወገኖች በርቀት የሚቀርቡ ሲሆን የተወሰኑ ደግሞ በአካል ይቀርባሉ) ይሰራሉ።  እባክዎን ከታች ያሉትን የፍርድ ቤት ክፍሎች ዝርዝር በፍርድ ቤቱ ከተመደቡ የችሎቶች አይነቶች ጋር ይመልከቱ፡

    - 113 – የሲ.ፒ.ኦ.፣ ኤ.ኤስ.ኦ.፣ ኢ.አር.ፒ.ኦ. መዝገቦች (በርቀት (ሪሞት))
    - 114 – የሲ.ፒ.ኦ.፣ ኤ.ኤስ.ኦ.፣ ኢ.አር.ፒ.ኦ. መዝገቦች (በርቀት (ሪሞት))
    - 117 – የዲ.ቪ.ኤም.፣ ሲ.ሲ.ሲ. እና ኢ.አር.ፒ.ኦ. መዝገቦች (ከሰኞ- ሀሙስ ቅይጥ ሲሆን አርብ ቀን ሙሉ በሙሉ በርቀት)
    - 118 – የዲ.ቪ.ኤም.፣ ሲ.ሲ.ሲ. እና ኢ.አር.ፒ.ኦ. መዝገቦች (ከሰኞ- ሀሙስ ቅይጥ ሲሆን አርብ ቀን ሙሉ በሙሉ በርቀት)
    - 119 –የቲ.ፒ.ኦ.፣ ቲ.ኤ.ኤስ.ኦ. እና የልጅ ቀለብ ጉዳዮች፣ የእስር ችሎቶች (ዲቴንሽን ሂሪንግስ) (ቅይጥ (ሀይብሪድ))
    - JM-9 – ተጠባባቂ የቲ.ፒ.ኦ.፣ ቲ.ኤ.ኤስ.ኦ. (በርቀት (ሪሞት))

<u>የወንጀለኛ መዝገቦች – የቤት ውስጥ ሁከት ቀላል-ወንጀል (ዶመስቲክ ቫዮለንስ ሚስደሚነር) (ዲ.ቪ.ኤም.) እና የፍርድ ቤት መድፈር ወንጀል (ክሪሚናል ኮንተምፕት) (ሲ.ሲ.ሲ.)</u>

- ሁሉም የከእስር የተፈቱ ተከላካዮች ችሎቶች **በርቀት ወይም በአካል** (እንደየ ቀረበው ማስታወቂያ) በተመደበላቸው ቀናን ሰአት በፍርድ ቤት ክፍል ቁጥር 117 እና በፍርድ ቤት ክፍል ቁጥር 118 መካሄድ ይቀጥላሉ። ይህም፣ ጉዳዩ ያለበት ደረጃ በሚታወቅበት ችሎቶች (ስታተስ ሂሪንግስ)፣ የእምነት ክህደት ቃል የሚሰጥባቸው ችሎቶች (አረይንመንትስ)፣ የዲ.ኤስ.ኤ. ግምገማ (ረቪው) እና የፍርድ ቀን፣ እና ምክኒያት አሳይ (ሶው ከውዝ) ችሎቶች፣ እና ሌሎች ያካተተ ይሆናል።

- በችሎቶች መቅረብ፡ የዲ.ሲ. ክፍል የፍርድ ቤት ክፍሎች መዝገቦችን በርቀት፣ ወይም እንደየ መዝገቡ በአካል መስማቱን ይቀጥላሉ። የዲ.ሲ. የፍርድ ቤት ክፍሎች ዳኞችና ጸሀፊዎች በአካል የሚቀርቡባቸው፣ እንደየ መዝገቡ የተወሰኑ አካላት በአካል ሲቀርቡ ሌሎቹ ደግሞ በርቀት የሚቀርቡባቸው ቅይጥ (ሀይብሪድ) ናቸው (ይህ የማይሆንበት የፍርድ ቤት ክፍሎቹ ሙሉ በሙሉ በርቀት በሚሆኑበት አርብ አርብ ነው)።

- ሁሉም የፍርድ ቤት ክፍሎች፣ የተከላካዮች፣ ምስክሮች፣ ተበዳዮች፣ ጠበቆች፣ የፍርድ ቤት ሰራተኞች፣ ጁረሮች እና ሌሎች የማህበረሰቡ አባላት ጤናና ደህንነት በሚጠብቅ መልክ በአካልና በርቀት ለማሳተፍ ተዋቅረዋል።

- **ከእስር ተፈተው ያሉ ተከላካዮች** እስከተቻለ ድረስ በቪድዮ መቅረብ ይችላሉ፣ በቪድዮ መቅረብ የማይችሉ ከሆነ ደግሞ፣ ፍርድ ቤቱ በአካል እንዲቀርቡ ካላዘዘ በስተቀር፣ በቴሌፎን መቅረብ ይችላሉ።

- ተከላካይ በርቀት የሚቀርብ ከሆነ፣ **የመንግስትና የተከላካይ ጠበቆችም** በርቀት በቪድዮ መቅረብ ይችላሉ።

- ተከላካይ በአካል የሚቀርብ ከሆነ፣ **የመንግስትና የተከላካይ ጠበቆችም** በአካል መቅረብ ይኖርባቸዋል።

- በግለሰብ መዝገብ በርቀት ምስክርነት እንዲሰጡ ፍርድ ቤቱ ካልፈቀደ በስተቀር በሁሉም ሂደቶች ያሉ **ምስክሮች** በአካል ይቀርባሉ።

- **የቅድመ ክርክር አገልግሎቶች (ፕሪትራያል ሰርቪስስ) እና የፍርድ ቤት አገልግሎቶች እና የበዳይ ክትትል ኤጀንሲ ተወካዮች** በአካል መሳተፍ ይችላሉ፣ ነገር ግን ከተቻለ በርቀት በቪድዮ፣ በቪድዮ መቅረብ የማይችሉ ከሆነ ደግሞ በቴሌፎን እንዲቀርቡ ይበረታታሉ።

- **የወንጀል ሰለባዎች** በአካል መሳተፍ ይችላሉ፣ ነገር ግን ከተቻለ በርቀት በቪድዮ ወይም በቴሌፎን እንዲቀርቡ ይበረታታሉ።

- የመያዝ አቅም ገደቦች ታሳቢ ባደረገ መልኩ **የማህበረሰቡ አባላት** በአካል መሳተፍ ይችላሉ፣ ነገር ግን ከተቻለ በርቀት በቪድዮ ወይም በቴሌፎን እንዲቀርቡ ይበረታታሉ።

- **የእምነት ክህደት ቃሎች (አረይንመንትስ)፡** የቤት ውስጥ ሁከት የእምነት ክህደት ችሎቶች (አረይንመንትስ) በፍርድ ቤት ቁጥር C-10 መሰማት ይቀጥላሉ። የሲ.ሲ.ሲ. የእምነት ክህደት ችሎቶች (አረይንመንትስ) በርቀት በሚካሄድ የዲ.ቪ.ዲ. የፍርድ ቤት ክፍል ይሰማሉ።

- **ምክኒያት አሳይ ችሎቶች (ሾው ከውዝ ሂሪንግስ)፡** በአካል፣ በከፊል በርቀት የሚካሄዱ የቅድመ-ክርክርና የብሮቤሽን ምክኒያት አሳይ (ሾው ከውዝ) ችሎቶች በዲ.ቪ.ዲ. የፍርድ ቤት ክፍል ከሰኞ እስከ ሀሙስ እለታት በዲ.ቪ.ዲ. የፍርድ ቤት ክፍሎች ይካሄዳሉ። ተቀባይነት ያለው የኮቪድ-19 ፕሮቶኮል ካለፉ በኋላ ተከላካዮች ዳኛው ፊት በአካል ይቀርባሉ። ተከላካይ በአካል የሚቀርብ ከሆነ፣ ፍርድ ቤቱ ሌላ ትእዛዝ ያስተላለፈ ካልሆነ በስተቀር፣ የተከላካይ ጠበቃ እና መንግስት በአካል መቅረብ ይኖርባቸዋል። ሁሉም ሌሎች ተከራካሪ ወገኖች ዳኛው እንደፈለገው በቴሌፎን ወይም በቪድዮኮንፈረንስ መቅረብ ይችላሉ።

- ሙሉ በሙሉ በርቀት የሚካሄዱ የቅድመ-ክርክርና የብሮቤሽን ምክኒያት አሳይ (ሾው ከውዝ) ችሎቶች በማንኛውም ቀን፣ ከሰኞ እስከ አርብ ሊቀጠሩ ይችላሉ። ተከላካዮች ጨምሮ ሁሉም ተከራካሪ ወገኖች በቴሌፎን ወይም በቪድዮኮንፈረንስ በርቀት መቅረብ ይኖርባቸዋል።

- የፕሮቤሽም ምክኒያት አሳይ ችሎቶች (ፕሮቤሽን ሾው ከውዝ ሂሪንግስ)፣ ፍርድ ቤቱ ሌላ ትእዛዝ ካላስተላለፈ በስተቀር በተቀጠረው ቀን በርቀት በሚካሄድ የፍርድ ቤት ክፍል ይካሄዳሉ። ኤ.ቪ.አር. ፋይል ማድረግ የፕሮቤሽኑ ማብቅያ ጊዜ ያቆመዋል (ቶል ያደርገዋል)።

- **ፍርድ ቤት ሲመጡ በፍርድ ቤት የእስር ማዘዣ እንዲታሰሩ የሚፈቅድ ማዘዣ (ዋክ-ኢን ቤንች ዋራንት) መዝገቦች፡** የፍርድ ቤት የእስር ማዘዣ የወጣላቸው ተከላካዮች ከ3:30 ፒ.ኤም. በፊት ለዲ.ቪ.ዲ. የጸሀፊ ቢሮ (ክለርክስ ኦፊስ) ራሳቸውን እጅ መስጠት ይችላሉ፣ የጸሀፊ ቢሮም (ክለርክስ ኦፊስ) በበኩሉ በቀኑ በተመደበው ዳኛ ፊት ለችሎት እንዲቀርቡ ያደርጋል።

- **የበእስር ያሉ ችሎቶች (ዲቴንሽን ሂሪንግስ)፡** የበእስር ያሉ ችሎቶች ተከላካዮች በ C-10 የእምነት ክህደት ቃላቸው በሚሰጡበት ጊዜ በፍርድ ቤት ክፍል ቁጥር 119 እንዲካሄዱ ቀነ ቀጠሮ ይሰጥባቸዋል። ችሎቶቹ በህግ በተደነገገው መመሪያ መሰረት ይዘጋጃሉ። በነዚህ መዝገቦች ያሉ ሁሉም ወገኖች በአካል መቅረብ ይኖርባቸዋል።

<u>የፍትሐብሔር መከላከያ ትዕዛዝ (ሲቪል ፕሮቴክሽን ኦርደር) (ሲ.ፒ.ኦ.ስ) መዝገቦች፣ የጸረ-ማሳደድ ትዕዛዝ (አንታይ-ስቶኪንግ ኦርደር) መዝገቦች፣ እና ከፍተኛ አደጋ መከላከያ ትዕዛዞች (ኤክስትሪም ሪስክ ፕሮቴክሽን ኦርደርስ) (ኢ.አር.ፒ.ኦ.ስ) መዝገቦች፡</u>

የቤት ውስጥ ሁከት ክፍል (ዶመስቲክ ቫዮለንስ ዲቪዥን)፣ በርቀት የሚካሄዱ ችሎቶች ለማቀላጠፍ ሁሉንም ተከራካሪ ወገኖች ሊገኙባቸው የሚችሉ እንደነ የቴሌፎን ቁጥሮችና ኢ.መይል አድራሻዎች የመሳሰሉ የመገኛ መረጃዎች ለመስጠት ጸሀፊ ቢሮን (ክለርክስ ኦፊስ) በቴሌፎን ቁጥር (202) 879-0157 ያገኙ ዘንድ ያበረታታል። እባክዎ፣ የገዛ ራስዎትን ወይም የተቃራኒ አካልን የመገኛ መረጃ ለመስጠት ወደዚህ የቴሌፎን ቁጥር ይደውሉ።

የፍትሐብሔር መከላከያ ትዕዛዝ (ሲቪል ፕሮቴክሽን ኦርደር) (ሲ.ፒ.ኦ.ስ) ጥያቄዎች፡

- የጊዜያዊ የፍትሐብሔር መከላከያ ትእዛዞች ጥያቄዎች በርቀት በሚሰማ ዳኛ (ሪሞት ጃጅ) ይሰማሉ። አዳዲስ የቲ.ፒ.ኦ. ጥያቄዎች ፋይል ከተደረጉ በኋላ ባሉ 2 ወይም 3 ሳምንታት አገልግሎታቸው ያበቃል።
- ተከራካሪ ወገኖች ቲ.ፒ.ኦ. እና ሌሎች ከጉዳዩ ተያያዥነት ያላቸው ወረቀቶች (እንደነ በሰው በኩል የፍርድ ቤት መጥሪያ ማድረሻ ሰነዶች)፣ በኢ.መይል ጭምር፣ በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ ይደርሳቸዋል። በአካል ፋይል አድራጊዎች፣ ፋይል ያደረጉዋቸውን ወረቀቶች ቅጂ በወረቀት እንዲሰጣቸው ከጸሀፊ ቢሮ (ክለርክስ ኦፊስ) መጠየቅ ይችላሉ።
- ሁሉም የሲ.ፒ.ኦ እና ተመሳሳይ መዝገቦች ጉዳዩ ፋይል ከተደረገ በኋላ ከሁለት ሳምንታት አከባቢ ይካሄዳሉ። በተጨማሪ፣ ተከራካሪ ወገኖቹ ከጠየቁና ፍርድ ቤቱም ክፍት ቦታ ካለው፣ ተከራካሪ ወገኖች የሲ.ፒ.ኦ. እና ኤ.ኤስ.ኦ. ጉዳያቸው ከተመደበው ቀን የቀረበ የችሎት ቀን እንዲሰጣቸው መጠየቅ ይችላሉ።

<u>አንድ አካል ብቻ ባለበት የተወሰኑ የሲ.ፒ.ኦ. መዝገቦች (ዲፎልት ሲ.ፒ.ኦ. ኬዝስ) የፍርድ ቤት የእስር ማዘዣዎች (ቤንች ዋራንትስ)፡</u> የፍርድ ቤት የእስር ማዘዣ የወጣላቸው መልስ ሰጭዎች (ሪስፖንደንትስ) በዛኑ ቀን በአካል ዳኛ ፊት ይቀርቡ ዘንድ በዲ.ቪ.ዲ. የጸሀፊ ቢሮ (ክለርክስ ኦፊስ) በ3:30 ፒ.ኤም. ራሳቸውን እጅ መስጠት ይችላሉ። ወይም የጸሀፊ ቢሮን በ (202-879-0157) በማግኘት የፍርድ ቤት የእስር ትእዛዝ በተመለከተ ለመነጋገር በርቀት የሚካሄድ ችሎት ቀጠሮ ማስያዝ ይችላሉ።

በሲ.ፒ.ኦ. ምክኒያት የተነሱ የልጅ ቀለብ (ቻይልድ ሳፖርት) መዝገቦች

- የቤት ውስጥ ሁከት ክፍል (ዶመስቲክ ቫዮለንስ ዲቪዥን) ወደ ክፍሉ የተመደቡ የልጅ ቀለብ መዝገቦች በምናባዊ የፍርድ ቤት ክፍል (ቨርቹዋል ኮርትሩም) ይሰማል።

ተከራካሪ ወገኖች ከተመደበው ቀነ ቀጠሮ በፊት ምናባዊው ችሎት (ቨርቹዋል ሂሪንግ) እንዴት መቀላቀል እንደሚቻል የሚያሳዩ ማስታወቂያና መመሪያዎች ያገኛሉ።

የጸረ-ማሳደድ ትዕዛዝ (አንታይ-ስቶኪንግ ኦርደር) መዝገቦች (ኤ.ኤስ.ኦ.ስ) ጥያቄዎች፡

- ጊዜያዊ የጸረ-ማሳደድ ትዕዛዝ (አንታይ-ስቶኪንግ ኦርደር) ጥያቄዎች መዝገቦች በርቀት በሚሰማ ዳኛ (ሪሞት ጃጅ)። አዳዲስ የቲ.ኤ.ኤስ.ኦ. ጥያቄዎች ፋይል ከተደረጉ በኋላ ባሉ 2 ወይም 3 ሳምንታት አገልግሎታቸው ያበቃል።
- ተከራካሪ ወገኖች ቲ.ፒ.ኦ. እና ሌሎች ከጉዳዩ ተያያዥነት ያላቸው ወረቀቶች (እንደነበራስ መንገድ ሰነዶቹን ለተከላካይ ማድረሻ ሰነዶች)፣ በኢመይል ጭምር፣ በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ ይደርሳቸዋል። በአካል ፋይል አድራጊዎች፣ ፋይል ያደረጉዋቸውን ወረቀቶች ቅጂ በወረቀት እንዲሰጣቸው ከጸሀፊ ቢሮ (ክለርክስ ኦፊስ) መጠየቅ ይችላሉ።
- ተከራካሪ ወገኖች ቲ.ኤ.ኤስ.ኦ. እና ሌሎች ከጉዳዩ ተያያዥነት ያላቸው ወረቀቶች (እንደነ በራስ መንገድ ሰነዶቹን ለተከላካይ ማድረሻ ሰነዶች)፣ በኢመይል ጭምር፣ በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ ይደርሳቸዋል።

ከፍተኛ አደጋ መከላከያ ትዕዛዞች (ኤክስትሪም ሪስክ ፕሮቴክሽን ኦርደርስ) (ኢ.አር.ፒ.ኦ.ስ) መዝገቦች ጥያቄዎች፡

- የኤክስ ፓርተ (አንድ አካል ብቻ) እና የመጨረሻ ኢ.አር.ፒ.ኦ.ስ ጥያቄዎች መደረግ ይችላሉ፣ እና በስራ ሰአታት በአካል በጸሀፊ ቢሮ (ክለርክስ ኦፊስ)፣ ወይም በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ ወደ DVD@dcsc.gov ኢመይል በማድረግም ፋይል መደረግ ይችላሉ። ማመልከቻው ከዲ.ሲ. ፍርድ ቤቶች ድረገጽ DC Courts website ማግኘት ይቻላል። የተመደበው ዳኛ ጉዳዩን በርቀት የፍርድ ቤት ክፍል ይሰማዋል።
- የማራዘሚያ አቤቱታ (ሞሽን ቱ ኤክስተንድ) ፋይል ካልተደረገ በስተቀር፣ ሁሉም ኢ.አር.ፒ.ኦ.ዎች በትእዛዙ ባለው ማብቂያ ቀን ተፈጻሚነታቸው ያበቃል።
- ሁሉም ኢ.አር.ፒ.ኦ.ዎች፣ ክርክሮችና ከኢ.አር.ፒ.ኦ. ተዛማጅነት ያለቸው አቤቱታዎች በግምት የመጀመሪያ ፋይል ከተረገ በኋላ ባሉ ጊዜያት በወረቀት በተቀመጠው ቀን ይሰማሉ። ተከራካሪ ወገኖች ከተመደበው ቀነ ቀጠሮ በፊት ምናባዊው ችሎት (ቨርቹዋል ሂሪንግ) በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ እንዴት መቀላቀል እንደሚቻል የሚያሳዩ ማስታወቂያና መመሪያዎች ያገኛሉ።
- ተከራካሪ ወገኖች የኤክስ ፓርተ (አንድ አካል ብቻ) እና ሌሎች ከመዝገብ-ጋር ተያያዥነት ያላቸው ወረቀቶች በኢመይል ጨምሮ በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ በኩል ይደርሳቸዋል። በአካል ፋይል አድራጊዎች፣ ፋይል ያደረጉዋቸውን ወረቀቶች ቅጂ በወረቀት እንዲሰጣቸው ከጸሀፊ ቢሮ (ክለርክስ ኦፊስ) መጠየቅ ይችላሉ።

# የቤተሰብ ፍርድ ቤት (ፋሚሊ ኮርት)

ተፈጻሚነታቸው ማለቅ የነበረባቸው በህጎች፣ በፍርድ ቤት ደንቦች፣ እና ፍርድ ቤት ባስተላለፋቸው እና በሌሎች ትዕዛዞች የሰፈሩ የጊዜ ገደቦች በዚህ የተወሰነ ጊዜ እንደሚከተለው ይታገዳሉ፣ ከተፈጻሚነት ለጊዜው ይቆማሉ (ቶል ይደረጋሉ)፣ ይራዘማሉም፡ በሁሉም የወጣት ጥፋተኛ ሀላፊነት አለመወጣት (ጁቨናይል ደሊኩዌንሲ)፣ ክትትል የሚያስፈልጋቸው ሰዎች፣ እና የግል ጉዲፈቻ መዝገቦች፣ በሁሉም የቤት ውስጥ ግንኙነት ቅርንጫፍ መዝገቦች፣[1] የወላጅነትና የድጋፍ (ፓረንቴጅ ኤንድ ሳፖርት) መዝገቦች እስከ 9፡00ኤ.ኤም. ጁን 27፣ 2022 ድረስ፣ ከዚህ ጊዜ በኋላ በዲ.ሲ. ኮድ እና በሱፐርየር ፍርድ ቤት ደንቦች ያሉ፣ ከታች ከተዘረዘሩት በስተቀር፣ የህግ እና ደምብ-መሰረት ያደረጉ የጊዜ ገደቦች በሙሉ ሀይል እና ውጤት ተፈጻሚ ይሆናሉ፣ ሁሉም የአእምሮ ጤና መዝገቦች እስከ 9፡00ኤ.ኤም. ጁላይ 11፣ 2022 ድረስ እና በዚህ ጊዜ በዲ.ሲ. ኮድ እና በሱፐርየር ፍርድ ቤት ደንቦች ያሉ የህግ እና ደምብ-መሰረት ያደረጉ የጊዜ ገደቦች በሙሉ ሀይል እና ውጤት ተፈጻሚ ይሆናሉ፣ ከዚህ ጊዜ በኋላ በህጎች፣ የፍርድ ቤት ደንቦች፣ እና ተፈጻሚ በሚሆኑ ትእዛዞች እና በሌሎች በፍርድ ቤት የተላለፉ ትእዛዞች ያሉ የሚከተሉት የጊዜ ገደቦች ብቻ ይህ ትእዛዝ ተፈጻሚ እስከሚሆንበት ጊዜ ድረስ ተንጠልጥለው፣ ከተፈጻሚነት ቆመው እና ተራዝመው ይቆያሉ፡ § 16–831.09 (የሶስተኛ አካል ባለአደራነት መዝገቦች እልባት ማግኛ የጊዜ ገደቦች) እና § 46-206 (የድጋፍ ችሎቶች ቀነ ቀጠሮ በማስያዝ ያሉ የጊዜ ገደቦች)።

ጠበቆችና ራሳቸውን የወከሉ ተከራካሪ ወገኖች ሰነዶችን በ https://dc.casefilexpress.com/Login.aspx በሚገኘው ኬዝፋይልኤክስፐረስ በመጠቀም በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ ፋይል ማድረግ ይችላሉ።

የጉዲፈቻ አቤቱታዎች (አዳፕሽን ፐቲሽንስ) በ https://dcscgov.app.box.com/f/aeaf4eb2153743519a495d3f95d26c93 በሚገኘው የዲጂታል መጣያ ሳጥን (ዲጂታል ድሮፕ ባክስ) በመጠቀም በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ ፋይል መደረግ ይችላሉ። ሁሉም ሌሎች በጉዲፈቻ መዝገቦች የሚደረጉ ልውውጦች በርቀት በኢ-ፋይሊንግ/ኬዝ ፋይል ኤክስፐረስ በኩል ፋይል ሊደረጉ ይችላሉ።

---

[1] ይህ የማይሆነው በሚከተሉት ነው፡ በዲ.አር.ቢ. መዝገቦች ጠበቃ እና ተከራካሪ ወገኖች በ60 ቀናት ውስጥ ሰነዶች ማድረስ፣ እና በተመደበው ዳኛ ትእዛዝ ያልተሰጠ ከሆነ፣ ሞሽኖች እና መቃወሚያዎች ፋይል ማድረግ ጨምሮ ከስርአታዊ ደንቦች የሰፈሩትን ማክበር ይጠበቅባቸዋል። ባለ እዳ ተብሎ ትእዛዝ ከተላለፈ በኋላ ለሚደረጉ ሞሽኖች የአገልግሎት ማድረሻ ማረጋገጫ በ60 ቀናት ውስጥ ፋይል አለማድረግ ጸሀፊ (ክለርክ) ጉዳዩ ዳግም ፋይል ማድረግ በሚፈቅድ መልኩ እንዲሰርዝ ሊያደርግ ይችላል።

በቤተሰብ ፍርድ ቤት የቤት ውስጥ ግንኙነቶች ቅሬታዎች ወይም አቤቱታዎች ፋይል የሚደረግበት ሂደት በፍርድ ቤቱ ድረገጽ በዝርዝር ይገኛል፣ https://www.dccourts.gov/sites/default/files/DRB-Case-InitiationInstructions-for-filers.pdf ይመልከቱ።

የቤተሰብ ፍርድ ቤት ራስ-አግዝ ማእከል (ፋሚሊ ኮርት ሰልፍ-ሄልፕ ሰንተር) በርቀት እና በአካል በመስራት ላይ ይገኛል። እርዳታ ለማግኘት እባክዎን ፍርድ ቤቱን ይጎብኙ ወይም (202-879-0096) ይደውሉ።

በደንብ 4 እና ደንብ 5 (Rule 4 and Rule 5) የሰፈረውን ምን ይሁን ምን፣ የቤት ውስጥ ግንኙነቶች መዝገቦች ያላቸው ተከራካሪ ወገኖች የፍርድ ቤት ሰነዶች ማህበራዊ ሚድያ ተጠቅመው ማድረሱን መቀጠል ይችላሉ። ግለሰቦች ሰነዶቹን በማድረስ ረገድ (በአካል ወይም ወደ ፖስታ ቤት በመሄድ የተረጋገጠ ፖስታ (ሰርቲፋይድ መይል)) ማህበራዊ ርቀት ለመጠበቅ እና "ትን ጥረት" የሚሉትን መስፈርቶች ላያሟሉ ስለሚችሉ፣ እና ይህ ሰነዶች የማድረሻ አማራጭ ዘዴ ትክክለኛውን ማስታወቂያ በማድረስ ረገድ ስኬታማነቱ ያረጋገጠ ስለ ሆነ፣ የጽሑፍ መልእክት (ቴክስት መሰጅ)፣ ኢመይል ወይም ሌላ የማህበራዊ ሚድያ ዘዴ ተጠቅሞ በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ ሰነዶች ማድረስ በደንብ Rule 4(c)(3)(B) መሰረት ተጨማሪ የፍርድ ቤት ትእዛዝ ሳያስፈልግ ተቀባይነት ይኖረዋል። መጥሪያው የሚያደርስ አካል ለተመደበው ዳኛ በሚያረካ መንገድ ማድረሱን ማረጋገጥ ይኖርበታል፣ በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ የተፈጸመው የማድረስ ዘዴ "ትክክለኛውን ማስታወቂያ ለመስጠት በምክንያታዊነት የተሰላ" መሆኑ የሚያሳይ መሆንን ያካትታል። በአካል ማድረስ በህግ፣ በዲ.ሲ. ኮድ §§ 13-332 (አቅመ አዳም ያልደረሱትን በአካል ማድረስ ያስገድዳል)፣ 13-333 (ብቁ ላልሆኑ (ኢንኮፐተንት) ሰዎች በአካል ማድረስ ያስገድዳል)፣ እና 46-206 (ድጋፍ (ሳፖርት) የተመለከቱ መዝገቦች በአካል ማድረስ ያስገድዳል) ጭምር፣ የተደነገገ ከሆነ ተከራካሪ ወገኖች በደንብ 4(c)(3)(B) መሰረት በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ ማድረስ አይችሉም።በሲፒርየር ፍርድ ቤት የቤት ውስጥ ግንኙነቶች ደንብ 5(d)(5)(B) መሰረት ፍርድ ቤቱ ተከራካሪ ወገኖች የፍርድ ቤት ሰነዶች ማድረሻ ቃለ መሀላ (አፊዳፊት ኦፍ ሰርቪስ ፕሮሰስ) በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ ፋይል እንዲያደርጉ ይፈቅዳል።

<u>በአካል የሚሰጡ አገልግሎቶች፡</u> የቤተሰብ ፍርድ ቤት የህዝብ ጽህፈት ቤቶች (ማእከላዊ መቀበያ ማእከል (ሰንትራል ኢንቴክ) ሰንተር፣ የቤት ውስጥ ግንኙነቶች፣ ወላጅነትና ድጋፍ፣ የወጣት ጥፋተኛ (ጁቨናይል) እና ቸልተኝነት፣ የአእምሮ ጤና እና ተሀድሶ፣ የልጅ ጉዳትና ቸልተኝነት ምክር፣ እና የጋብቻ ቢሮ ያጠቃለለ) በአካል አገልግሎት ለመስጠት ክፍት ይሆናሉ። የቤተሰብ ፍርድ ቤት በተጨማሪ በኢፋይሊንግ በኩል የተላኩ ሰነዶችን ሂደት ማድረጉ ይቀጥላል። አስቸኳይ መዝገቦች ለምዘና ወደ ዳኛ ይላካሉ፣ እና አብዛኛዎቹ ችሎቶች በርቀት ይካሄዳሉ። እባክዎን፣ ሁሉም የአስቸኳይ መዝገቦች ከአመት በአሎች በስተቀር ከሰኞ እስከ አርብ ከ4፡00

ፒ.ኤም. በፊት ፋይል መደረግ እንደሚኖርባቸው ልብ ይበሉ።

የጋብቻ ቢሮ በርቀት እና በአካል ስራውን በማከናወን ይገኛል። የተፋጠነ አገልግሎት ለማግኘት ደምበኞች የተረጋገጡ ቅጂዎች (ሰርቲፋይድ ካፒስ) ጥያቄዎች በአካል እንዲያደርጉ ይበረታታሉ።

የቤተሰብ ፍርድ ቤት ካላንደሮች በተመለከተ ዝርዝር መረጃ ለማግኘት እባክዎን ድረገጻችን https://www.dccourts.gov/superior-court/family-court-operations ይጎብኙ

## የግብር (ታክስ)፣ እና የኑዛዜ ማረጋገጫ (ፕሮቤት) ክፍሎች

በግብር (ታክስ)፣ እና በኑዛዜ ማረጋገጫ (ፕሮቤት) ክፍሎች የነበረ እግድ አሁን ተነስቷል፣ እና በዲ.ሲ. ኮድ እና በሱፒርየር ፍርድ ቤት ደንቦች ያሉ ሁሉም የህግና ደንብ-ተኮር የጊዜ ገደቦች ባሁኑ ሰአት በሙሉ ሀይል ተግባር ላይ ይውላሉ።

በአካል የሚደረጉ አገልግሎቶች፡

- የግብር (ታክስ)፣ እና የኑዛዜ ማረጋገጫ (ፕሮቤት) ክፍሎች የህዝብ አገልግሎት ባንኮዎች (ካውንተሮች) ሰነዶችን በአካል ፋይል ማድረግ ለሚፈልጉ ወይም መዝገቦችን በአካል ማየት ለሚፈልጉ ሰዎች የሚፈልጉትን ያደርጉ ዘንድ ከሰኞ እስከ አርብ ከ 8:30 ኤ.ኤም. እስከ 5:00 ፒ.ኤም. ክፍት ናቸው።
- የኑዛዜ ማረጋገጫ ራስ-አግዝ ማእከል (ፕሮቤት ሰልፍ-ሄልፕ ሰንተር) (ProbateSelfHelpCenter@dcsc.gov) የጣልቃ ገብነት ሂደቶችና (ኢንተርቬንሽን ፕሮሲዲንግስ) አነስተኛ ርስት በተመለከተ ፋይል የሚደረጉ ነገሮች (ስሞል ኢስቴት ፋይሊንግስ) ፋይል በማድረግ ዘንድ መረጃና እርዳታ ለመስጠት በአካል አገልግሎት ለማቅረብ ክፍት ነው። ማእከሉ በተጨማሪ በርቀት በ(ProbateSelfHelpCenter@dcsc.gov) አገልግሎት ለመስጠት ክፍት ነው።

በርቀት የሚደረጉ አገልግሎቶች፡

- አገልግሎቶች በርቀት መሰጠት ይቀጥላሉ፣ በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ ፋይል ማድረግም ይቀጥላል። ሁሉም ተቀጥረው ያሉ ችሎቶች በርቀት ይካሄዳሉ። በአካል እንዲቀርቡ በዳኛው ካልታዘዙ በስተቀር ማናቸውም ተከራካሪ ተከራካሪ ወገኖች ወይም ጠበቆች በአካል መቅረብ የለባቸውም። ከኦገስት 15፣ 2022 ጀምሮ ሁሉም በኑዛዜ ማረጋገጫ ክፍል የሚካሄዱ ክርክሮች በህንጻ A በአካል መካሄድ ዳግም ይጀምራሉ።

የኑዛዜ ማረጋገጫ ክፍል (ፕሮቤት ዲቪዥን) እንደሚከተለው ይሰራል፡

- ዳኞች የሚከተሉትን መዝገቦች በርቀት በዌብኤክስ ይሰማሉ፡
    - የ21-ቀን አስቸኳይ ሞግዚቶች (ኢመርጀንሲ ጋርድያንስ)— በኢመይል (ጠበቆችና ራሳቸውን-የወከሉ ፋይል አድራጊዎች) ፋይል የተደረጉ፣ ወይም በአካል ፋይል የተደረጉ።
    - የ90-ቀን የጤና-ጥበቃ ሞግዚቶች (ሄልዝ-ኬር ጋርድያንስ)— በኢመይል (ጠበቆችና ራሳቸውን-የወከሉ ፋይል አድራጊዎች) ፋይል የተደረጉ፣ ወይም በአካል ፋይል የተደረጉ።
    - የአጠቃላይ የፍርድ ቤት ሂደት ማመልከቻዎች (ፐቲሽንስ ፎር ጀነራል ፕሮሲዲንግስ) (የሞግዚትነት እና ተንከባካቢነት ማመልከቻዎች (ጋርድያን ኤንድ ኮንዘርቫቶርሺፐ ፐቲሽንስ)) – በኢመይል (ጠበቆችና ራሳቸውን-የወከሉ ፋይል አድራጊዎች) እና በፖስታ (ራሳቸውን-የወከሉ ፋይል አድራጊዎች) ፋይል የተደረጉ፣ ወይም በአካል።
    - ዳኛው ዌብኤክስ በመጠቀም በርቀት ሊሰሙ ይችላሉ ብሎ የወሰነባቸው ሌሎች የጣልቃገብነት መዝገቦች (ኢንተርቬንሽን ማተርስ)
    - ዳኛው በዌብኤክስ በመጠቀም በርቀት ሊሰሙ ይችላሉ ብሎ የወሰነባቸው የንብረት መዝገቦች (ኢስቴት ኬዝስ) ጨምሮ፣ ሌሎች የኑዛዜ ማረጋገጫ መዝገቦች
- በርቀት ለሚካሄዱ ችሎቶች፣ የአዳዲስ መዝገቦች ፋይል ማድረጎች እና የፍርድ ቤት ትእዛዞችና የክፍል ማስታወቂያዎች መድረስ ለማቀላጠፍ የኑዛዜ ማረጋገጫ ክፍል ሁሉንም ተከራካሪ ወገኖች ፋይል ስለ ተደረጉ መዝገቦች በተመለከተ፣ እንደነ ተከራካሪ ወገኖች ሊገኙባቸው የሚችሉ የቴሌፎን ቁጥሮችና ኢመይል አድራሻዎች የመሳሰሉ፣ የመገኛ መረጃዎች እንዲያቀርቡ ያበረታታል።
- የሞግዚትነት ቀጠሮዎች ሶስት ዓመታዊ ግምገማዎች በጃንዋሪ 2፣ 2022 መካሄድ ይቀጥላሉ።
- ወርሃዊ የዎርድ ጉብኝት መስፈርቶች ተግባራዊ እንደሆኑ ይቆያሉ።

የኑዛዜ ማረጋገጫ ክፍል (ፕሮቤት ዲቪዥን) አገልግሎቶች በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ቢፈልጉ እባክዎን የኑዛዜ ማረጋገጫ ክፍል (ፕሮቤት ዲቪዥን) አሰራሮች ማስታወቂያ ይመልከቱ። https://www.dccourts.gov/superior-court/probate-division

የግብር ክፍል (ታክስ ዲቪዥን) እንደሚከተለው ይሰራል፡

- ምክኒያት አሳይ (ሾው ከውዝ)፣ ጉዳዩ ያለበት ሁኔታ (ስታተስ ሂሪንግ) ችሎቶች፣ እና የመጀመሪያ የመርሀግብር (ኢኒሻል ስኬጁሊንግ) ኮንፈረንሶች በርቀት በዌብኤክስ በመጠቀም ይካሄዳሉ። የቅድመ-ክርክር ኮንፈረንሶች እና ክርክሮች ዳኛው ካላዘዘ በስተቀር በአካል ይካሄዳሉ።

- ሽምግልናዎች በርቀት በ Zoom.gov ይካሄዳሉ።

- በርቀት የሚካሄዱ ችሎቶችና ሽምግልናዎች ለማቀላጠፍ፣ በሁሉም ፋይል የሚደረጉ ሰነዶች ተከራካሪ ወገኖች ሊገኙባቸው የሚችሉ የቴሌፎን ቁጥሮችና ኢመይል አድራሻዎች የመሳሰሉ፣ የመገኛ መረጃዎች እንዲያቀርቡ የግብር ክፍል ያበረታታል።

- ራሳቸውን የወከሉ ተከራካሪ ወገኖች ፋይል ለሚያደርጓቸው ማመልከቻዎች (ፕሊዲንግስ) ወይም የማመልከቻዎቹ ምስል ወደ TaxDocket@dcsc.gov በኢመይል መላክና ፋይል ማድረጊያ ክፍያ በቼክ ወይም ማኒ ኦርደር ወደ D.C. Superior Court, Tax Division, 500 Indiana Ave., NW, Suite 4100, Washington, DC 20001 መላክን መቀጠል ይችላሉ።

## <u>የኦዲተር ማስተር ቢሮ</u>

ኦዲተር ማስተሩ ሁሉንም ችሎቶች በርቀት በዌብኤክስ በኩል እያካሄደ ነው። ተከራካሪ ወገኖች በቪድዮ-ኮንፈረንስ፣ በቪድዮ-ኮንፈረንስ ለመሳተፍ የሚያስችል ቴክኖሎጂ የሌላቸው ከሆነ ደግሞ በቴሌፎን መሳተፍ ይችላሉ። በርቀት እንዴት መሳተፍ እንዳለብዎ የሚያሳዩ መመሪያዎች ለሁሉም ተከራካሪ ወገኖች ይሰጣሉ። የዲ.ሲ. ፍርድ ቤቶች የኮምፒውተር መሳርያዎች ወይም የኢንተርኔት አገልግሎት ለሌላቸው ሰዎች በተቀጠረው ችሎት እንዲሳተፉ የሚያስችሉ የርቀት ችሎት ቦታዎች (ሪሞት ሂሪንግ ሳይትስ) አሉት። ለችሎትዎ የርቀት ችሎት ቦታዎች ለመጠቀም የሚፈልጉ ከሆነ ችሎትዎ ከመድረሱ ቢያንስ ከ24 ሰዓታት በፊት በርቀት ተደራሽነት የሚያስችል ኮምፒውተር ለመያዝ በ(202) 879-1900 ዘንድ ይደውሉ ወይም ወደ DCCourtsRemoteSites@dcsc.gov ኢመይል ይላኩ። በአካል የሚደረጉ ችሎቶች ሞሽን በማድረግ ሊካሄዱ ይችላሉ።

ኦዲተር ማስተሩ ከኦገስት 1፣ 2020 ጀምሮ ያስተላለፋቸውን ሁሉም ትዕዛዞች ተከራካሪ ወገኖች ማክበር ይኖርባቸዋል። ቢሮው ባሁኑ ሰአት አስቀድመው ተቀጥረው የነበሩ የሁሉንም ችሎቶች ሌላ ቀነ ቀጠሮ የሚሰጥ ትዕዛዝ፣ በአዳዲስ መዝገቦች የችሎቶች ቀነ ቀጠሮ፣ እና ሰነዶች የሚቀርቡባቸው አዳዲስ ቀናት የያዙ የተለያዩ ትዕዛዞችን በመስጠት ይገኛል። ቢሮው ሁሉንም አስቀድሞ ቀጠሮ ተይዞላቸው የነበረ ችሎቶች ሌላ ቀጠሮ የሚያስይዙ ትእዛዞች አስተላልፏል። ለአዳዲስ ጉዳዮች ችሎቶች ለመቅጠር፣ እንዲሁም ደግሞ ሰነዶች የሚረከቡባቸው ቀናት የሚወስኑ ትእዛዞች እየተሰጡ ይገኛሉ።

ሰራተኞች (ስታፍ) በርቀት ከ8:30 ኤ.ኤም. እስከ 5:00 ፒ.ኤም. ከሰኞ እስከ አርብ ይገኛሉ። ሰራተኞች ሁሉንም ሰነዶች በርቀት ሂደት እያደረጉ እንደሆነ ልብ ይበሉ። ሰነዶች በኢመይል ለAuditor.Master@dcsc.gov ወይም በፖስታ ለ፡ Office of the Auditor-Master, 500 Indiana Avenue NW, Washington, DC 20001 ማስረከብ ይችላሉ። በሚስጢር መያዝ የሚኖርባቸው (ሰንሲቲቭ ኢን ኔቸር) ሰነዶች በኢመይል በኩል ወደ AMFinancialBox@dcsc.gov መላክ ይቻላል። ሰነዶች በቴሌፎን ቁጥር (202) 626-3280 በመደወል ቀጠሮ በማስያዝ ብቻ ወደ ቢሮ ማስረከብ ይቻላል።

ሁሉም ችሎቶች የተደረጉባቸውና ሁሉም ሰነዶች የተረከቡባቸው መዝገቦች በተመለከተ ሪፖርቶች በመዘጋጀት ይገኛሉ። ሪፖርቶች እንደተጠናቀቁ ለተከራካሪ ወገኖች እንዲደርሱ ይደረጋሉ።

ጥያቄዎች ቢኖርብዎ እባክዎ ቢሮውን በቴሌፎን ቁጥር 202-626-3280 ወይም በኢመይል በAuditor.Master@dcsc.gov ያግኙ።